# ኢትዮጵያ፡- የለጋሾች ዕርዳታ አፈናን ያባብሳል

**ለጋሾች የልማት ፕሮግራሞችን መፈተሽና የሚለግሱትን ገንዘብ አጠቃቀም መከታተል አለባቸው።**

(ለንደን፡ ጥቅምት 9 ቀን 2003 ዓ.ም.) - የኢትዮጵያ መንግስት ለገዢው ፓርቲ ድጋፍ መስጠትን በመንግስት የሚካሄዱ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ለመሆን እንደሚያስችል ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ የልማት ዕርዳታን የፖለቲካ ተቃውሞን ለማፈን እየተጠቀመበት እንደሚገኝ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዛሬ ባወጣው ሪፖርት አስታወቀ። ሂዩማን ራይትስ ዎች የውጭ ለጋሾች የሚሰጡት ዕርዳታ ተጠያቂነትና ግልጽነት ባለው መልኩ ሥራ ላይ መዋሉንና የፖለቲካ አፈናን ለመደገፍ እንዳልዋለ እንዲያረጋግጡ ጠይቆአል።

105 ገፆች ያሉትና "ልማት ያለ ነፃነት፡ ዕርዳታ አፈናን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዴት እንደሚደግፍ" በሚል ርዕስ የወጣው ይኸው ሪፖርት የኢትዮጵያ መንግስት ከለጋሾች የሚያገኘውን ሀብት በስልጣን ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) ስልጣን ለማጠናከር እንዴት እንደሚጠቀምበት ይዘረዝራል።

በድርጅቱ የአፍሪካ ዳይሬክተር የሆኑት ሮና ፔሊጋል እንደሚሉት "የኢትዮጵያ መንግስት ዕርዳታን ዜጎችን ለመቆጣጠርና የፖለቲካ ተቃውሞን ለመደፍጠጥ ይጠቀምበታል፤ የገዢውን ፓርቲ ጨዋታ ለማይጫወቱ በሩ ዝግ ነው። ሆኖም ግን የውጭ ለጋሾች ይህንን የኢትዮጵያ መንግስት ጸባይ በየጊዜው እያደገ በሚሄድ ዕርዳታቸው እያበረታቱ ነው።"

ኢትዮጵያ በዓለም ከፍተኛ የልማት ዕርዳታ ተቀባይ ከሆኑ ሀገሮች ውስጥ አንዷ ነች። እ.ኤ.አ በ 2008 ዓ.ም ብቻ ከሦስት ቢልዮን ዶላር በላይ በዕርዳታ አግኝታለች። የዓለም ባንክ እና ለጋሽ ሀገራት እንደ ጤና፣ትምህርት፣ግብርና እና የውሃ አቅርቦት ያሉ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያስችል ቀጥተኛ የበጀት ድጋፍ ለወረዳ መስተዳድሮች ያደርጋሉ። ከዚህ በተጨማሪም በከፋ ድህነት ውስጥ ለሚገኙ የሀገሪቱ ዜጎች ለሚሰጠው 'ምግብ ለሥራ' ለሚባለው ፕሮግራም ድጋፍ ይሰጣሉ። የአውሮፓ ኅብረት፣ዩናይትድ ስቴትስ፣ብሪታኒያ እና ጀርመን ዋነኞቹ የሁለትዮሽ ትብብር ለጋሾች ናቸው።

የምግብ ዕርዳታ በእጅጉ የሚያስፈልጋቸውን የገጠር ነዋሪዎች ጨምሮ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ደጋፊዎችና የሲቪል ማኅበረሰብ መሪዎች በመንግስት ከሚካሄዱ ፕሮግራሞች ድጋፍና ዕርዳታ እንዳያገኙ በአካባቢ ባለሥልጣናት ይከለከላሉ። የሀገሪቱን ልማት ለማፋጠን ተብሎ በውጭ ለጋሾች ድጋፍ የሚካሄዱ 'የአቅም ግንባታ' ፕሮግራሞች ተማሪዎችን የገዢውን ፓርቲ ርዕዮተዓለም እንዲቀበሉ ለመስበክ፣መምህራንን ለማዋከብና ነፃ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸውን ሠራተኞች ከሲቪል ሰርቪሱ ለማስወገድ ሥራ ላይ እየዋሉ ነው።

ይህ ፖለቲካዊ አፈና በተለይ በግንቦት ወር 2002 በሀገሪቱ ተካሂዶ ገዢው ፓርቲ በፓርላማ ካሉ መቀመጫዎች ውስጥ 99.6 በመቶውን ያሸነፈበት ምርጫ ከመካሄዱ አስቀድሞ በነበሩት የመዳረሻ ጊዜያት በኃላ መልኩ ተስተውሎአል።

ምንም እንኳን በመንግስት ክልከላ ምክንያት በዚህ ጉዳይ ላይ ነፃ ጥናት ማካሄድ አስቸጋሪ ቢሆንም ሂዩማን ራይትስ ዎች እ.ኤ.አ በ 2009 በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በሦስት ክልሎች በሚገኙ 53 መንደሮች ውስጥ የሚኖሩ ከ 200 በላይ ነዋሪዎችን ቃለ መጠይቅ አድርጓል። በዚህም ችግሩ በሰፊው የሚስተዋል መሆኑን ለመረዳት ችሎአል።በብዙ አካባቢዎች ነዋሪዎቹ አድልዎ እንደሚፈጸምባቸው ለሂዩማን ራይትስ ዎች ገልጸዋል።

አርሶ አደሮች የገዢው ፓርቲ ደጋፊ ባለመሆናቸው ብቻ ለግብርና ሥራ የሚሆኑ ዕርዳታዎች፣አነስተኛ ብድሮች፣የዘር እህል እንዲሁም ማዳበሪያ እንዳያገኙ መደረጋቸውን ገልጸዋል። በአማራ ክልል የሚኖሩ አንድ አርሶ አደር ለሂዩማን ራይትስ ዎች ሲናገሩ "የአካባቢ ባለሥልጣናት የተቃዋሚ ደጋፊዎችን ለይተው እንደሚያወጡና ምንም ዓይነት ልዩ ጥቅም እንዳያገኙ እንደሚያደርጉ በይፋ ተናግረዋል።ይህም ማለት ማዳበሪያ፣የሴፍቲ ኔት እንዲሁም የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታም ቢሆን አያገኙም ማለታቸው ነው።" ብለዋል።

የገጠር ነዋሪዎቹ እንደገለጹት የተቃዋሚ አባላት የሆኑ በርካታ ቤተሰቦች በጣም ተጎጂ ለሆኑ 7 ሚሊዮን ዜጎች ድጋፍ በሚደረግበት የምግብ ለሥራ ወይም የሴፍቲ ኔት ፕሮግራሞች እንዳይሳተፉ ተደርገዋል። በአካባቢ ባለሥልጣናት እነዚህን አገልግሎቶች እንዳያገኙ የተከለከሉ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት

ክልከላውን አስመልክቶ ቅሬታቸውን ለገዢው ፓርቲና ለመንግስት ባለሥልጣናት በሚያቀርቡበት ወቅት የሚሰጣቸው ተመሳሳይ ምላሽ "የራሳችሁን ፓርቲ እንዲረዳችሁ ጠይቁ" የሚል ነው።

በተጨማሪም በውጭ መንግስታት የገንዘብ ድጋፍ በሚካሄደው የአቅም ግንባታ ፕሮግራም ሥር የገዢው ፓርቲ ርዕዮተዓለም በሚሰበክባቸው ስብሰባዎች እንዲሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣መምህራንና ሠራተኞች እንዴት እንደሚገደዱ የሚያሳዩ መረጃዎችን ሂዩማን ራይትስ ዎች አሰባስቦአል። በእነዚህ ስብሰባዎችና የስልጠና መድረኮች የተሳተፉ ሰዎች የገዢው ፓርቲ አባል ካልሆናችሁ በሚል ዛቻና ማስፈራሪያ እንደደረሰባቸው ገልጸዋል። የበላይ ኃላፊዎች የደረጃ ዕድገትና የስልጠና ዕድል ለማግኘት የገዢው ፓርቲ አባል መሆን ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ለመምህራን ይነግራሉ። የትምህርቱ ዘርፍ በተለይም ትምህርት ቤቶችና የመምህራን ስልጠና ሰፊ የለጋሾች የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው መስኮች ናቸው።

"መንግስትን በሁሉም ደረጃዎች በበላይነት በመቆጣጠር ገዢው ፓርቲ ሁሉንም የዕርዳታ ፕሮግራሞች ይቆጣጠራል።" በማለት የሚገልጹት ፔሊጋል "ውጤታማ እና ነፃ የሆነ የክትትል ሥራ የማይኖር ከሆነ፣ ዓለማቀፍ ዕርዳታ ያለአግባብ ጥቅም ላይ መዋሉንና ጨቋኝ የሆነ የአንድ ፓርቲ ሥርዓትን ለማጠናከር ድጋፍ ማድረጉን ይቀጥላል።" ብለዋል።

በርካታ የተቃዋሚ መሪዎችን ወህኒ እንዲወርዱ፣30 ሺህ የሚሆኑ ሰዎች በቁጥጥር ሥር እንዲውሉና 200 ሰዎች እንዲገደሉ ምክንያት የሆነውን የ 1997 ድህረ ምርጫ የመንግስት ርምጃ ተከትሎ የዓለም ባንክ እና ሌሎች ለጋሾች ለኢትዮጵያ መንግስት የሚያደርጉትን ቀጥተኛ የበጀት ድጋፍ አግደዋል። በወቅቱም ገዢው ፓርቲ የዕርዳታውን ገንዘብ ለፖለቲካ ዓላማ ሊያውለው ይችላል የሚል ስጋት እንደነበራቸው ገልጸው ነበር።

ይሁንና ብዙም ሳይቆይ ዕርዳታው "የመሠረታዊ አገልግሎቶች ጥበቃ" በሚል አዲስ ፕሮግራም ሥም እንዲቀጥል ተደርጓል። ይህ የዕርዳታ ማዕቀፍ ዕርዳታ በቀጥታ ለወረዳ መስተዳድሮች እንዲተላለፍ የሚደረግበት ነው። እነዚህ የወረዳ መስተዳድሮች እንደ ፌደራል መንግስቱ ሁሉ በገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ሥር ከመሆናቸውም በላይ ለቁጥጥርና ለክትትል ሥራ የበለጠ አስቸጋሪ ናቸው። በመሆኑም በሕዝቡ ላይ የሚደርሰውን የዕለት ተዕለት አፈና ቀጥተኛ አስፈጻሚዎች ናቸው።

በዚሁ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግስት የፖለቲካ ምህዳሩን ቀስ በቀስ ዘግቶአል፣ነፃ ጋዜጠኞችን አሳዶአል፣ የሲቪል ማኅበረሰብ መሪዎችን ድምጽ እንዲታፈን ወይም ለስደት እንዲዳረጉ አድርጓል፤ እንዲሁም የመደራጀትና ሐሳብን በነፃ የመግለጽ መብቶች ጥሷል። እ.ኤ.አ በ2009 የጸደቀው የሲቪል ማኅበራት ሕግ ከ 10 በመቶ በላይ ገቢያቸውን ከውጭ ምንጮች የሚያገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሰብአዊ መብቶች፣ከመልካም አስተዳደር እና ከግጭት አፈታት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ሥራዎችን እንዳይሰሩ ከልክሏል።

"የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክትትል ሥራ ይሰሩ የነበሩት ጥቂት ነፃ ድርጅቶች በመንግስት በሚፈጸምባቸው ማዋከብና ገዳይ በሆነ የሲቪል ማኅበራት ሕግ ሳቢያ ከስመዋል። እነዚህ ድርጅቶች ግን ዕርዳታ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ እጅግ አስፈላጊ ነበሩ።" ብለዋል ፔሊጋል።

በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ እየከፋ በሄደ ቁጥር ለጋሾች ዕርዳታቸውን ጨምረዋል። እ.ኤ.አ ከ 2004-2008 ባሉት ዓመታት ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ዓለማቀፍ የልማት ዕርዳታ በእጥፍ አድጓል። እንደኢትዮጵያ መንግስት መረጃ ከሆነ ሀገሪቱ ድህነትን በመቀነስ ረገድ አበረታች ርምጃ እያሳየች ነው። እናም ለጋሾች ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን የሚሊኒየም የልማት ግቦች ለማሳካት የምታደርገውን ርምጃ በደስታ ይደግፋሉ። ይሁን እንጂ ለዚህ ርምጃ የሚከፈለው ዋጋ ከፍተኛ ነው።

ሂዩማን ራይትስ ዎች የጥናት ውጤቶቹን ለለጋሽ ሀገራት ባለሥልጣናት በሚያቀርብበት ጊዜ ብዙዎቹ እየከፋ የሄደውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታና የገዢውን. ፓርቲ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ አምባገነናዊ ባሕርይ አንደሚገነዘቡ በግል በሚደረጉ ውይይቶች ወቅት ይገልጻሉ። በርካታ የምዕራብ ሀገራት መንግስታት የዕርዳታ ድርጅቶች ባለሥልጣናትም በለጋሾች የሚደገፉ ፕሮግራሞች የፖለቲካ አፈናን ለማራመድ እየዋሉ ነው የሚሉ ክሶች እንዳሉ እንደሚያውቁ ፣ነገር ግን የችግሩ ስፋት ምን ያህል እንደሆነ የሚያውቁበት ምንም መንገድ የሌላቸው መሆኑን ለሂዩማን ራይትስ ዎች ገልጸዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ በለጋሾች የሚደገፉ ፕሮግራሞች ላይ የሚደረጉ የክትትልና የቁጥጥር ሥራዎች በአብዛኛው የሚከናወኑት ከኢትዮጵያ መንግስት ባለሥልጣናት ጋር በጋራ በመሆን ነው።

ያም ሆኖ ከግብር ከፋዮቻቸው የሚገኘው ገንዘብ ላልተገባ ሥራ ጥቅም ላይ ሊውል ስለሚችልበት ሁኔታ ያላቸውን ሥጋት በይፋ ለመናገር ፈቃደኛ የሆኑ ብዙ ለጋሾች የሉም። የለጋሾች ስብስብ የሆነው የልማት ዕርዳታ ቡድን የተሰኘው አካል ለሂዩማን ራይትስ ዎች በሰጠው በመስከ ጥናት ላይ ያልተደገፈ ምላሽ ቡድኑ በሚሰጠው ዕርዳታ ድጋፍ የሚደረግላቸውን ፕሮግራሞች አፈጻጸም የሚከታተልበት ሥርዓት ፕሮግራሞቹ በትክክል እየተካሄዱ እንደሆነና ዕርዳታው ለሌላ ተግባር እንዳልዋለ እንደሚያሳይ ገልጾአል። ይሁንና አንድም ለጋሽ በጉዳዩ ላይ ነፃ እና ተአማኒ የሆነ ጥናት አላደረገም።

ሂዩማን ራይትስ ዎች የለጋሽ ሀገራት ሕግ አውጪ አካላትና የቁጥጥር ተቋማት ለኢትዮጵያ የሚሰጠው የልማት ዕርዳታ የፖለቲካ አፈናን ለማካሄድ እየዋለ እንዳልሆነ እንዲመረምሩ ጥሪ አቅርቦአል።

"ኢትዮጵያ ውስጥ መሻሻል እንዳለ ለማሳየት ካላቸው ጉጉት የተነሳ የዕርዳታ ባለሥልጣናት ይፋዊ ከሆነው የመንግስት ስታትስቲክስ ጀርባ ያደፈጠውን አፈና ላለማየት ዐይናቸውን ጨፍነዋል፤ የኢትዮጵያን መንግስት በገንዘብ የሚደግፉ ለጋሾች ካሸለቡበት በመንቃት የሚሰጡት ዕርዳታ ሰብአዊ መብቶች እንዲጣሱ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን ማየት ይኖርባቸዋል።" ብለዋል ፔሊጋል።

### *ደጋፊ መረጃዎች*

በ 1983 ዓ.ም የመንግስቱ ኃይለማርያምን ወታደራዊ መንግስት በማስወገድ ሥልጣን የያዘው ገዢው ፓርቲ ብሔርን መሠረት ያደረጉ ፓርቲዎች ኅብረት ሲሆን በሕዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ (ሕወሃት) የሚመራ ነው። መንግስት በ 1987 ዓ.ም መሠረታዊ የሰብአዊ መብቶችን ያካተተ ሕገ መንግስት ያጸደቀ ቢሆንም በተግባር ግን እነዚህ ነፃነቶች ባለፉት 19 ዓመታት በየጊዜው እየተገደቡ ሄደዋል። ምንም እንኳ በ 1983 ሥልጣን እንደያዘ መንግስት የመድብለ ፓርቲ ምርጫን ቢያስተዋውቅም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ቢሮዎችን ለመክፈትና ለማደራጀት እንዲሁም በብሔራዊና የአካባቢ ምርጫዎች ወቅት በነፃ ተንቀሳቅሰው የምርጫ ዘመቻ ለማካሄድ ከባድ እንቅፋቶች ይገጥሟቸዋል።

85 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በገጠር የሚኖር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከ 10 እስከ 20 በመቶ የሚሆነው በየዓመቱ በዓለምአቀፍ የምግብ ዕርዳታ ላይ ጥገኛ ነው። ለኢትዮጵያ መንግስት የሚሰጠው የውጭ የልማት ዕርዳታ ከኤርትራ ጋር ከ 1990-1992 ዓ.ም በተደረገው የድንበር ጦርነት ወቅት ለጊዜው ጋብ ከማለቱ በስተቀር በ 1990 ዎቹ በየጊዜው እየጨመረ ሄዶአል። በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ከዓለም ባንክ እና ከውጭ መንግስታት ከፍተኛውን ዕርዳታ በመቀበል ከአፍሪካ ቀዳሚዋ ነች።

እ.ኤ.አ በ 2008 ለኢትዮጵያ የተሰጠው ጠቅላላ ዕርዳታ 3.3 ቢሊዮን ዶላር ነበር። ከዚህ ውስጥ ዩናይትድ ስቴትስ 800 ሚሊዮን ዶላር ያዋጣች ሲሆን በአብዛኛው ለሰብአዊና ለምግብ ዕርዳታ ነው። የአውሮፓ ኅብረት 400 ሚሊዮን ዶላር ሲያዋጣ ብሪታንያም 300 ሚሊዮን ዶላር አዋጥታለች። ድህነት ቅነሳን የሚመለከተውን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሚሊኒየም የልማት ግቦች ለማሳካት ኢትዮጵያ መልካም ርምጃዎች እያሳየች መሆኑ በሰፊው የሚገለጽ ነው። ይሁንና ይህንን የሚመለከቱ መረጃዎች በአብዛኛው ከመንግስት የሚወጡና በነፃ ወገኖች ያልተረጋገጡ ናቸው።

### ከሪፖርቱ የተወሰዱ ጥቅሶች

"ሁሉም ሰው የሚወስዳቸው አነስተኛ ብድሮች አሉ፤ ሆኖም ግን ለእኛ የተቃዋሚ አባላት በጣም አስቸጋሪ ነው። 'ይህ ከእናንተ መንግስት የመጣ አይደለም፣ ከምትጠሉት መንግስት የተገኘ ነው። የምትጠሉት መንግስት የሆነ ነገር እንዲያደርግላችሁ ለምን ትጠብቃላችሁ?' ይሉናል።" - አንድ አርሶ አደር ከደቡብ ክልል

"ትናንትና እንኳ የቀበሌው ሊቀመንበር 'ብዙ ችግር እየደረሰብህ ነው፤ ለምን ተጸጽቻለሁ የሚል ማመልከቻ ጽፈህ ገዢውን ፓርቲ አትቀላቀልም?' አለኝ።" - በረሀብ የተጠቃ ልጅ ያለውና በደቡብ ክልል በምግብ ለሥራ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዳይሆን የተከለከለ አንድ አርሶ አደር

“የሴፍቲኔት ፕሮግራም ለገዢው ፓርቲ ታማኝነትን ለመግዛት እየዋለ ነው። ይህ ገንዘብ ከውጭ የሚመጣ ነው፤ ዲሞክራሲ ከውጭ በሚመጣ ገንዘብ እየተሸረሸረ ነው። ለመሆኑ ገንዘቡን የሚልኩት ሠዎች ገንዘቡ ለምን ሥራ እየዋለ እንደሆነ ያውቃሉ? ዲሞክራሲን ለማጥቃት እየዋለ እንደሆነ ንገሯቸው።”- አንድ አርሶ አደር ከአማራ ክልል

“ገንዘባችን የፖለቲካ ተከታዮችን የማፍራት ሥራ ለመስራት እየዋለ መሆኑ ግልጽ ነው።”- አንድ የዋነኛ ለጋሽ አማካሪ፣ አዲስ አበባ

“ማስፈራራትና ማዋከብ በሁሉም ስፍራዎችና አካባቢዎች ይታያል። የቤቶች ሥራ፣ የንግድ፣የትምህርት፣የግብርና ሥራዎች ፖለቲካዊ ገጽታ ይሰጣቸዋል። ብዙ ሠዎች ሴፍቲኔትና የመሳሰሉትን ለማግኘት ገዢውን ፓርቲ እንዲቀላቀሉ ይገደዳሉ ወይም ጫና ይደርስባቸዋል። ብዙዎቹ ሌላ ምርጫ የላቸውም፤ ተገደው ነው።”- አንድ የምዕራብ ሀገር የዕርዳታ ባለሥልጣን፣ አዲስ አበባ

“በእጃቸው ያለውን መሣሪያ ሁሉ፡ ማዳበሪያ፣ ብድር፣ ሴፍቲኔት ተቃዋሚዎችን ለመደፍጠጥ እየተጠቀሙበት ነው። ይህንን እናውቃለን።”- አንድ የምዕራብ ሀገር ከፍተኛ የዕርዳታ ባለሥልጣን፣ አዲስ አበባ

“የትኛውን መንግስት እንዴትስ ነው እየገነባን ያለነው? የምንገነባው የመንግስትን የመቆጣጠርና የማፈን አቅም ሊሆን ይችላል።”- አንድ የዓለም ባንክ ሠራተኛ፣ አዲስ አበባ

**ሙሉ ሪፖርቱን “ልማት ያለ ነፃነት፡ ዕርዳታ አፈናን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዴት እንደሚደግፍ” ለማንበብ ይህንን ድረ ገፅ ይጎብኙ፡** http://www.hrw.org/node/93605